በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጤና ሚኒስቴር

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጤና ሚኒስቴር

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት በፋይናንስ አዋጁ፣ ደንቡ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሰረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2014 በጀት ዓመት የተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 980/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዓለም አቀፍ ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው።

እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል።

የተጠቃለሉት የሂሳብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ፣ አጥጋቢ ማረጋገጫና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በተጠቃለሉት የሂሳብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ በሪፖርቱ ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ይሁን የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች

ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የተጠቃለለውን የሂሳብ ሪፖርት ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ ያቀረባቸው የተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በህክምና ኮሌጁ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው።

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን ወስዶ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ የተዘጋጁ የተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶች፡-

- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣
- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የካፒታል ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ የ2015 የሂሣብ ሪፖርቶችጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩሽን የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

1. <u>ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>

1.1 በአቤት ሆስፒታል የስራ ባህሪ አንጻር የአስክሬን ክፍል ሰራተኛ እና የላውንደሪ ክፍል የሚሰሩ ሰራተኞች ዘላቂነት ያለው በመሆኑ በመዋቅር ውስጥ የስራ መደቡ ቋሚ ሰራተኞች እንዲኖረው ያልተደረገ መሆኑ እና በበጀት ዓመቱ ለኮንትራት ሰራተኞች በድምሩ ብር 460,800.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ

1.2 በቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ አይሲዩ፣ ኢንፎርሜሽን ኮምንኬሽን፣ የማህበራዊ ጉዳይ ክፍል እና የአይን ኦፐራሲዮን ለሚሰሩ ሰራተኞች ዘላቂነት ያለው በመሆኑ በመዋቅር ውስጥ ለስራ መደቡ ቋሚ ሰራተኞች እንዲኖረው ያልተደረገ መሆኑ እና በበጀት ዓመቱ ለኮንትራት ሰራተኞች በታዩ ስምንት (8) ቫውቸሮች ብር 10,803,042.66 ክፍያ የተከፈለ መሆኑ

2. <u>የሕጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Issues)</u>

2.1 በአቤት ሆስፒታል ለአቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ (Prepayment to supplier) ብር 1,995,227.11 ከአንድ ዓመት በላይ ሳይወራረድ በተሰብሳቢነት ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ

2.2 በአቤት ሆስፒታል ሁለንተናዊ አበዳሪ (Sundry creditor) በሚል የሚታየው ብር ብር 1,765,230.89 በወቅቱ ያልተከፈለ ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት የቆየ ሂሳብ መኖሩ

2.3 ወራቤ ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል ከተለያዩ የእለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች የተሰበሰበ በድምሩ ብር 16,964,218.41 በሞ/64 ሳይጠቃለል ለገንዘብ ያዥ በቀጥታ የተሰበሰበበት ደረሰኝ የሚተላለፍ መሆኑ

2.4 በወራቤ ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል ከውስጥ ገቢ እንዲጠቀም በበጀት ዓመቱ የሆስፒታሉ ቦርድ የወሰነበት ውሳኔ ቢቀርብም ተራፊውን ገንዘብ የጤና ተቋማቱ ከዓመታዊ የበጀት ጥያቄ ጋር አቅርበው የውስጥ ገቢው በመንግሥት ሲታወጅ ለፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ማዋል ሲገባቸው ከበጀት ጥያቄ ጋር ለመንግስት ሳያሳውቁ በባንክ ሂሳብ ቁጥር 000091639363 ብር 77,670,017.85 ገቢ የተደረገ የሚታይ መሆኑ

2.5 በወራቤ ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል ስም ሳይሆን በስልጤ ልማት ማህበር ስም ተዘጋጅቶ የቀረበ የመብራት መክፈያ ደረሰኝ መሰረት በድምሩ ብር 467,141.58 ክፍያው የተፈጸመ መሆኑ

2.6 ወራቤ ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል ከአንድ ወር አስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 183,579.70 እና ከአንድ ዓመት በላይ አስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ

ቅድሚያ ክፍያዎች ብር 23,743.83 በድምሩ ብር 207,323.53 በወቅቱ ሳይወራረዱ በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ

2.7 በወራቤ ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 610,109.81 ከአንድ ዓመት በላይ አስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 327,780.67 በድምሩ ብር 856,285.79 በወቅቱ ሳይከፈል ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ መሆኑ

2.8 በቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከአንድ ወር እስከ አንድ አመት የቆየ ብር 446,361,783.53 እንዲሁም ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት የቆየ ብር 309,991,221.98 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ

2.9 በቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከአንድ ወር እስከ አንድ አመት የቆየ ብር 322,113.10 እንዲሁም ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት የቆየ ብር 6,820,253.56 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ

3. ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

3.1 በአቤት ሆስፒታል

❖ **የመ/ቤቱ ለመደበኛ ስራ የሚያገለግሉ ንብረቶች**

- በበጀት ዓመት የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከወጪ ቀሪ ያልተመዛዘነ መሆኑ፤
- በግቢው ውስጥ ታሽጎ የተቀመጠ የንብረቱ አይነት እና ከመቼ ጀምሮ እንደተቀመጠ የማይታወቅ ከመሆኑም በላይ በማን እንደሚጠበቅ የማይታወቅ በመሆኑ ንብረቱን ለማየት ያልተቻለ መሆኑ፡-
- ንብረቶች አገልግሎት ይስጡ ወይም አይስጡ የማይታወቅ በሆስፒታሉ በረንዳዎች ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ መልኩ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- ከለጋሽ አካላት የሚሰጡና ተገዝተው የሚገቡት የተለያዩ ቋሚና አላቂ ንብረቶች ተለይተው ተመዝግበው የማይያዙና ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣

❖ **የመድሃኒት ማስቀመጫ ግምጃ ቤት ውስጥ**

- በሆስፒታሉ ሶስት የመድሃኒት ግምጃ ቤት የንብረት ያዥ እና የንብረት መዝጋቢ በአንድ ሰዉ የሚሰራው መሆኑ፤
- የመድሃኒት ግምጃ ቤት ውስጥ የመድሀኒት አቀማመጡ ሲታይ የመድሀኒቶች በየአይነታቸው ለእይታ እና በቀላሉ ለማግኘት በሚያመች መልኩ ያልተቀመጡ ከመሆኑም በላይ አንዱ በአንዱ ተደራርቦና ተከማችቶ የተቀመጠ እና የክፍሉ

የአየር ሁኔታም መድሃኒቶች በቀላሉ እንዲበላሽ የሚዳርግ መሆኑ ቢን ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም መድሀኒቶች ሲወጡና ሲገቡ የማይመዘገብበት እና ከወጪ ቀሪ የማያሳይ መሆኑ፤-

- የመድሃኒት ገቢ እና ወጪ በኢፍሚስ (IFMIS) ሲስተም የማይደረግ መሆኑ
- የመጠቀምያ ጊዜያቸዉ ያለፈ የተለያዩ አይነት መድሃኒቶች በግምጃቤት ዉስጥ ተከማችቶ መገኘቱ፤
- የመጠቀምያ ጊዜያቸዉ ያለፈና አገልግሎት የሚሰጡ መድሃኒቶች በአንድ ላይ የተቀመጡ ከመሆኑም በላይ ባመመዝገባቸው ብዛታቸውን ለማወቅ ያልተቻለ የተለያዩ ብረታ ብረቶች በመድሐኒት ግምጃ ቤት ዉስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ

❖ **የህክምና መገልገያ መሳሪያ ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ**

- የህክምና መገልገያዎች (supplies) ጥቅም ላይ ያልዋሉ እንደ ሲሪንጆች እና የዕቃዎቹን ዓይነት መለየት ያልተቻለ በካርቶን ታሽገው ከግምጃ ቤት ዉጪ ተቀምጠው የሚገኙ ንብረቶች መኖሩ፤
- የንብረት ክፍል ባለሞያ ንብረት ሲወጣ እና ሲገባ እንዲሁም ከወጪ ቀሪ የሚከታተልበት ቢን ካርድ እንዲሁም የንብረት ወጪና ገቢ መመዝገቢያ (እስቶክ) ካርድ ለንብረቶቹ ያልተዘጋጀ መሆኑ
- የህክምና መሳሪያዎች በየአይነታቸው ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ያልተቀመጡ መሆናቸው፤
- ሁለት ግምጃ ቤትና ሁለት ኮንቴነር ውስጥ ያሉ የህክምና መገልገያ ንብረቶች የንብረት ያዥ እና የንብረት ገቢ እና ወጪ ሰራተኛ በአንድ ሠራተኛ የሚሰራ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በሆስፒታሉ ከሚገኙ የታርጋ ቁጥር 4-20034፣4-14364 እና 4-00485 ተሽከርካሪዎች ባለቤትነታቸው የጤና ጥበቃ የሆኑ እና በሆስፒታሉ ስም ያልሆነ መሆኑ
- ከ2013 ዓ/ም ጀምሮ አገልግሎት መስጠት ያቆሙ ሁለት (2) የታርጋ ቁጥር. 4-15361 እና 4-32733 ተሽከርካርዎች የሚገኙ መሆኑ በኦዲት ወቅት ማወቅ ተችሏል፡፡

3.2 ወራቤ ኮምፕሬንሲቭ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፡፡

- በቋሚ ግምጃ ቤት የስቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ባላንስ ሲታይ በአካል ካለ ጋር የማይመሳከር እና ወቅታዊ አለመሆን፤

- የአገልግሎት የማይሰጡ ቋሚ ንብረቶች ከመቼ ጀምሮ እንደተቀመጡ የማይታወቅ እና ሳይወገዱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ
- የሰሌዳ ቁጥር 4-21668፣ 4-13598፣ 4-02448 እና 4-00448 ተሽከርካሪች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር በሌላ መሥሪያ ቤት ሥም (ደቡብ ክልል ጤና ቢሮ፣ ሀ.ሀ ዩኒቨርስቲ፣ ስልጤ ዞን ጤና ቢሮ እና ስልጤ ልማት ማህበር) ተመዝግበው የሚገኙ መሆኑ

3.3 በቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ

- ✓ በ2015 በጀት ዓመት የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ

የራስ እምሩ የህትመት ማዕከልን በተመለከተ

- ✓ በንብረት ክፍል ውስጥ እንዲወገዱ ያልተደረጉ በቆይታ ብዛት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ዋና ዋና የውስጥ እቃዎች የጎደሉ በርካታ ኮምፒዩተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ እና የተለያዩ ብረቶች ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ በንብረት ክፍል ውስጥ መቼ ተገዝተው እንደገቡ የማይታወቅ በርካታ ለህትመት ስራ የሚያገለግሉ (ሪም) ወረቀቶች ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ በህትመት ማእከሉ በሁሉም እስቶር ዉስጥ የንብረት ርክክብ ሳይደረግ በአዲስ የንብረት ሠራተኛ የተተካ መሆኑ፣
- ✓ ከ2008 ዓ/ም ጀምሮ የሚል የታተሙ በርካታ ለተለያዩ የህትመት ዉጤቶች በኮንቴነር ዉስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ ፤
- ✓ በማተሚያ ቤት የታተሙ የህትመት ዉጤቶች መስፊያ ማሽን (Bostich 7011 canalogy full color and c-800 full color) እና ሌሎች በቁጥር 6 የፕሪንቲንግ ማሺኖች በብልሺት የቆሙና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ ፤
- ✓ የርክክብ ቬርቫል የሌላቸውና ከመቼ ጀምሮ እንደተከማቸ ማስረጃ ሊቀርብላቸው ያልቻሉ የሚወገዱ ንብረቶች ሳይወገዱ በስቶር ዉስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ በጳውሎስ ሆስፒታል ሚ/ሜ/ኮለጁ ለስድስት ተቋማት በስጦታ የተላለፉ ንብረቶች በመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ ተረጋግጠ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ሳይቀርብ በኮሚቴ ውሳኔ ብቻ የተሰጠ መሆኑ

የመድሃኒት ግምጃ ቤት

- ✓ የመድሃኒት ግምጃ ቤቱ ለመድሃኒት ማስቀመጫነት ጠባብ በመሆኑ እና አየር እንደ ልብ የማይገባ የጣራ እርቀት የሌለው በመሆኑ በሙቀት መድሃኒቶች

ለብልሽት ሊዳረግ የሚችል መሆኑ እና ጣራው የተቀደደ በመሆኑ ዉሃ የሚያፈስ መሆኑ፣

- ✓ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ እስከ ኦዲቱ መጨረሻ ያልተወገዱና ለሆስፒታሉ ስራአመራር ሪፖርት የተደረገ በርካታ መድሃኒቶች መኖራቸው፣
- ✓ በተለያዩ መጋዘንና ከመጋዘን ውጪ ለዝናብና ለፀሐይ ተጋልጠው የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ያሉ እና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ያልተወገዱ መሆኑን
- ✓ ሶስት/3 /ተሽከርካሪዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የማይገኙ በቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ኮሌጅ ግቢ ዉስጥ ያለምንም መጠለያ ለፀሐይ፣ ለዝናብ እና ለአቧራ ተጋልጠው ቆመዉ መሆኑ

<u>ባለፉት በጀት ዓመታት የሂሳብና የንብረት የኦዲት ግኝቶች</u>

<u>አቤት ሆስፒታል</u>

የ2013 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት

- ለሁለት ሰራተኞች በትምህረት ደረጃቸዉ ከተፈቀደላቸዉ የማበረታቻ አበል ክፍያ መጠን በላይ የተከፈለ ሳይመለስ የሚታይ ቀሪ ብር 7,291.84 መኖሩ
- የማበረታቻ አበል ክፍያ ላልተፈቀደላቸዉ የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች የተጣራ ተከፋይ ብር 7,542,468.40 የልዩ አበል ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡
- ለአቶ ሀይሌ መርጋሳ ከሃምሌ 2010 ዓ .ም ጀምሮ ከተፈቀደው ዉጭ በየወሩ ብር 900.00 እና ብር 1,500.00 በጠቅላላው ብር 47,000.00 እንዲከፈላቸዉ የተደረገ መሆኑ
- ለአቶ ሀይሌ መርጋሳ የሆስፒታሉ የአስተዳደርና ልማት ዳየሬክተር ተሿሚዎች በተፈቀዳው የደመዎዝ ጭማሪ መሰረት አላግባብ ብር 98,352.00 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ

የ2011 በጀት ዓመት

- ሁሉም ሾፌሮች ከፍተኛው የሾፌሮች አበል በወር ብር 800.00 ታስቦላቸው ሾፌሮቹ ሰርቪስም አምቡላንስም ደርበው ሰርተዋል በሚል በወር ለአንድ ሾፌር 1,600.00 በመከፈሉ ምክንያት በጠቅላላው ብር **136,800.00** ከመመሪያ ዉጪ አለአግባብ ክፍያ እንዲፈጸም የተደረገ መሆኑ፤

- የችግኝ ተከላ ፕሮግራም በቢሾፍቱ ለአንድ ቀን የተካሄደ በመሆኑ የወሎ አበል ክፍያው የቁርስና የምሳ ውሎ አበል ብቻ መፈጸም ሲገባው የሶስት ቀን ውሎ አበል በመፈጸሙ ምክንያት ያለአግባብ ብር 46,674.45 ክፍያ የተፈጸ መሆኑ

ወራቤ ኮምፕሬንሲቭ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

በ2011 በጀት ዓመት ግኝት መሰረት

- በአዲስ አበባ እና በሌሎች በተለያዩ በሀገር ውስጥ የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች በመመሪያ ከተፈቀደው ዉጪ ያለአግባብ ክፍያ ብር 163,000.00 ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- የውሎ አበል ክፍያ በጠቅላላው ብር 4,998.00 የተፈጸመ ሲሆን ከመጡበት መሥሪያ ቤት ውሎ አበል አለመውሰዳቸውን የሚያረጋግጥ እና ክፍያው በወራቤ ሆስፒታል በኩል እንዲፈጸም የተጻፈ ደብዳቤ ሳይኖር ሆስፒታሉ የውሎ አበል ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

2010 **በጀት ዓመት**

- የሆስፒታሉ አንድ ፖንዳ ሞተር ሳይክል ሊብሬና ታርጋ የሌለው መሆኑ፤

በቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ

- በወራቤ ኮምፕርሂንሲቭ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የተማሪዎች መኖሪያ ሕንፃ ግንባታ ፕሮግራም ኦሪክስ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር (Orrix Construction P.L.C) ቀድሞ ሥራው ሲጀመር ቅድመ ክፍያ (Advance Payment) ተከፍሎ ያልተመለሰ ብር 3,909,270.71 እና በውሉ መሰረት ሥራውን ባለመስራቱ ቅጣትና ወለድ ብር 3,861,076.51 በጠቅላላ ድምር ብር 7,770,348.22 በኮሌጁና በኮንትራክተሩ መሀከል በተደረገው ክርክር ፍርድ ቤቱ በቀን 30/06/2014 ዓ.ም በፍ/ይ/መ/ቁ.213970 የተወሰነ ቢሆንም የፍርድ አፈፃፀሙ ያልተጠናቀቀ ፡፡
- ላልተፈቀዱ የሥራ መደቦች የተፈጸመ የኮቪድ አበል ክፍያ፤ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በትምህርት ደረጃቸው ከተፈቀደላቸው በላይ የማበረታቻ አበል ክፍያ መጠን በላይ ብር 130,050.00 ክፍያ ከተፈጸመው ውስጥ ብር 73,650.00 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪ ብር 56,400.00 ይሆናል፤
- በአቤት ሆስፒታል ለሁለት ሰራተኞች በትምህርት ደረጃቸው ከተፈቀደላቸው በላይ የማበረታቻ አበል ክፍያ መጠን በላይ ብር 36,900.00 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- በአቤት ሆስፒታል የአመራር ማትጊያ አበል ክፍያ የጤና ባለሙያ ላልሆነ ለሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ በየወሩ ብር 1,500.00 ክፍያ እንዲፈጸም

የተፈቀደ ቢሆንም የሆስፒታሉ የአስተዳደርና ልማት ዋና ዳይሬክተር ለሆኑት ለአቶ ኃይሌ መገርሳ ከሐምሌ 2010 ዓ.ም ጀምሮ ከተፈቀደው ውጪ በየወሩ ብር 900.00 እና ብር 1,500.00 በጠቅላላው ብር 47,400.00 እንዲከፈላቸው የተደረገ መሆኑ፤

- የወራቤ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የኮንትራት ቅጥር ሰራተኞች በሚል ለተመሳሳይ ወራቶች ወርሃዊ ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓትና የኃላፊነት አበል ክፍያ ብር 1,564,746.29 አለአግባብ ከፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር በ2014 583,121.39 በ2015 ብር 942,757.16 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 38,867.74 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የማበረታቻ ክፍያ እንዲፈጸም በመንግሥት ሳይወሰን እና ለዚሁ ክፍያ ተብሎ የተፈቀደ በጀት ሳይኖር በበጀት ዓመቱ ውስጥ አለአግባብ ክፍያ ከተፈጸመው ብር 46,091.56 ውስጥ ብር 41,591.56 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ብር 4,500.00 ከአቶ ቃልኪዳን ገ/ጻዲቅ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ለህክምና ሰራተኞቹ የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጸም በጂንካ የውሎ አበል ተመን መሰረት መፈጸም ሲገባው በአዋሳ የውሎ አበል ተመን በመከፈሉ ምክንያት ያለአግባብ ብር 8,000.00 በብልጫ ተከፍሎ ከተገኘው ውስጥ ብር 3,528.00 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 4,472.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

በሜዲካል ኮሌጁ ሰራተኞች ሲለቁ በሥራ ላይ በነበሩበት ወቅት ይገለገሉበት የነበረውን ቋሚ ዕቃ ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ ስለማድረጋቸው

- በተለያየ ምክንያት ሰራተኞቹ መሥሪያ ቤቱን ሲለቁ በእጃቸው ይገኝ የነበረውን በጠቅላላው ብር 228,021.26 ዋጋ የሚያወጡ ላፕቶፕ ኮምፒተርና ሌሎች እቃዎች ስለመመለሳቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ከ2009 በጀት ዓመት ቀጠራ በፊት ሁለት ዋጋቸው ብር 27,892.87 ሆኑ ላፕቶፕ ኮምፒዊተሮች በሰራተኞች እጅ እያሉ የጠፉ መሆናቸው የተገለጸ ቢሆንም ኮሌጁ ሁኔታውን አጣርቶ ንብረቶቹን ለማስመለስ ተገቢው ጥረት ያልተደረገ መሆኑ፤

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

መጋቢት 2016 ዓ.ም